ስለ-ሺ Sileesua

ቅጽ ፩ ቁጥር ፩ መስከረም ፳፻፲፫




“ፍፁም የመሰለ መጥፎ ዕጣ በሕይወቴ ለትልቁ መልካም አጋጣሚ በር ከፈተልኝ”

“እኔ ትምህርት ቤት መሄዴን እንደ ዕድለኝነት እቆጥረዋለሁ”

እሷ የትነበርሽ ንጉሴ

@Sileesua
@Sileesuabot



ስለ - ሷ | Sileesua

ስለ-ሷ በየወሩ የኣርኣያዎችን ጥንካሬ ፣ ፈተና እና ስኬት ይዛ ወደ አንቺ የሚትቀርብ ህትመት ናት። ስለ-ሷ ሴትነትን ከፍ በማድረግ ከህልማቸው እና ከስኬታቸው የደረሱ ተምሳሌቶችን ታርክ በይዘታቸው አስውባ ለአንባቢዎቿ ታቀርባለች።

ስለ-ሷ ስለ-አንቺ ትቀርባለች!

ስለ - ሷ ዝማኔች ለማግኘት

@Sileesua

@Sileesuabot



ሎሬየት የትነበርሽ ንጉሴ

እሷ የትነበርሽ ንጉሴ የተወለደችው ጥር 24 ቀን በ1985ዓ.ም ሲሆን በሰድስት ዓመትዋ ባጋጠማት ህመም ምክንያት የዓይን ብርሃኗን አጣች። ይህ ክስተት ለእርሷም ሆነ ለቤተሰቦቹ እጅግ አስደንጋጭ ሁኔታ ነበር። በተለይ በተወለደችበት የገጠራማ መንደር የነበረው ድንጋጤ ከባድ ነበር ፤ ምክንያቱም በዚያች መንደር ዓይነ ስውር ለመሆን ሰበቡ የፈጣሪ ዕጣ ወይም አንዳች እርግማን እንደነበር ነው የታመነው። በመንደርተኞቹ ዓይን እንደኃጢአተኛ መቆጠር ብቻ ሳይሆን ያላትን ዋጋና ስፍራም ጭምር ነበር ያጣችው። በመንደሩ የምትኖር ሴት ልጅ ዕጣ ፈንታ ማግባትና ለቤተሰቦቿ ጥሎሽ ረብጣ ማስገኘት ነው። እናም እሷን ማንም ወንድ ሊያገባት እንደማይፈልግ እርግጥ ነበር። "ይህ ፍፁም የመሰለ መጥፎ ዕጣ በሕይወቴ ለትልቁ መልካም አጋጣሚ በር ከፈተልኝ።" ትላለች አጋጣሚው ቤተሰቦቿን ለትምህርት ወደ አዲስ አበባ እንዲልኳት ያስገደደ በመሆኑ።

በወቅቱ በአድስ አበባ ለዓይነ ስውራን የሚሆን ትምህርት ቤት ባለመኖሩ ወደ ሻሸመኔ ተልካ እስከ ስድስተኛ ክፍል በከፍተኛ ውጤት ተምራ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰች። በአዲስ አበባ ዳግማዊ ምንሊክ ትምህርት ቤት ከሰባተኛ እስከ አሰራ ሁለተኛ የነበረውን ትምህርቷን ተከታተለች። በትምህርት ቤቱ በመጀመሪያ ዓመታቶች የገጠማት ፈተና ከባድ ነበር። እሷም ስለ ጊዜው በተናገረችበት ወቅት "ከዚህ በፊት ከአሰራ ስድስት እስከ ሃያ ተማሪዎች ብቻ ባሉበት ክፍል እማር የነበርኩት ልጅ በአንዴ ከሰባ ልጆች ጋር ስቀላቀል ገሃነም የጣሉኝ ነበር የመሰለኝ። በዚያ ላይ አይነስውር በመሆኔ እኔን ለማቅረብ ፈቃደኞች አልነበሩም።" ብላለች። ተማሪዎች እንዲህ ቢያገኟትም አልቀሳና ተለማምጣ እንዲቀርቧት ከማድረግ ይልቅ በትምህርቷም ሆነ ባሏት የተለያዩ ችሎታዎች ተጠቀማ ያራቃትን ማህበረሰብ ለማቅረብ ተነሳችና ድንቅ ብቃቷን አስመሰከረች።

ተማሪዎችም እሷን እንደ አርአያቸው ከማድረግ ባለፈ እንደርሷ ለመሆን ይመኙ ጀመር። እሷም በድንቅ ብቃትዋ በመቀጠል በትምህርት ቤቱ ውስጥ የተማሪዎች መማክርት ምክትል ፕሬዝዳንትና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ፣ የሙዚቃ ባንዱ ድምፃዊ ፣ የስነፅሁፍ ክፍሉ ገጣሚ በመሆን በሁሉም እውቅናን አተረፈች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንዳጠናቀቀች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት በመማር ከመጀመሪያዎቹ ሴት ዓይነ ስውራን የሕግ ባለሙያዎች መካከል አንዷ ሆነች። ኋላ ላይም ትምህርቷን በመቀጠል በሶሻል ዎርክ ይትምህርት መስክ ሁለተኛ ዲግሪዋን ለመስራት በቅታለች።

እሷ ለበርካታ አካል ጉዳተኞች ብርሃን እና ጉልበታቸው ሁናለች። ጊዜዋን ዕድል ላላገኙ በርካታ አካል ጉዳተኞች የዕድል በራቸውን ለመክፈት እና መብቶቻቸውን ለማስከበር ከላይት ፎር ዘ ወርልድ የተባለ መንግስታዊ ካልሆነ ዓለም አቀፍ ድርጅት ጋር በበርካታ ስፍራዎች ድምጿን አሰምታለች። ከዚህ በተጨማሪም በኢሲዲዲ ውስጥ በስራ አስኪያጅነት እየመራች አካል ጉዳተኞችን የልማት አጋር ማድረግ ላይ ሰፊ ሥራ በመስራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጋለች።

እሷ ስለ ታሪኳ እና ሴት አካል ጉዳተኞች ከዓመታቶች በፊት በሪፖርተር ጋዜጣ እንዲህ ስትል ጽፋለች "የግል ታሪኬ ደስ

የሚልና አነቃቂ ቢሆንም ምን ያክል ያልተለመደ እንደሆነና መታደል የታከለበት እንደሆነ ሰዎች ልብ እንዲሉት እፈልጋለሁ። ለበርካታዎች በደሃ አገር ለሚኖሩ አካል ጉዳተኛ ሕፃናት ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘትና ትምህርት ቤት መሄድ ይዘት የሚመጣውን መልካም አጋጣሚ ማግኘት እጅግ እጅግ ከባድ ነው።

ይህን በቁጥር ማስረጃ አስደግፎ ማስረዳት ከባድ ነው፤ ምክንያቱም ከአካል ጉዳተኞች ጋር የተያያዙ መረጃዎች ማግኘት ሌላው ትልቁ ችግር ነውና። ሆኖም በአዳጊ አገሮች የሚኖሩ ሠላሳ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ አካል ጉዳተኛ ሕፃናት ትምህርት ቤት እየሄዱ እንዳልሆነ ይገመታል። ይህ ቁጥር ከሰዊድን ሕዝብ አጠቃላይ ብዛት ሦስት እጥፍ በላይ ነው።

በተለይ ደግሞ በገጠር ለሚኖሩ አካል ጉዳተኛ ልጃገረዶች ሕይወት እጅግ ፈታኝ ነው። ከሴትነታቸው ጋር አካል ጉዳታቸው ሲጨመር ሊያልፉት የሚገባቸው መሰናክልና እንቅፋት በእጅጉ ብዙ እና አታካች ነው። ሁሌም በሕይወት ሠልፍ ውስጥ ከመጨረሻዎቹ መጨረሻ የሚገኙት አካል ጉዳተኛ ሴቶች ናቸው። የእነርሱን ታሪክም በደንብ አጥርቼ አውቀዋለሁ። ቤት ውለው ታናናሽ ወንድምና እህቶቻቸውን እንዲንከባከቡ የሚወሰንባቸው እኒሁ ሴቶች ልጆች ናቸው።

እነርሱን በአግባቡ ለማስተማር የሚረዱ ግባዓቶች የሉንም በሚል እና ሌላም ምክንያት ‹‹መስማት የተሳናቸውንና ዓይነ ስውራን ተማሪዎችን አንቀበልንም›› በሚል ከትምህርት ቤት ደጃፍ የሚመለሱት ወላጆች የእኒሁ ሴቶች ወላጆች ናቸው። ክራንች አሊያም ደግሞ ዊልቼር በማጣት ወደ ትምህርት ቤት የሚወስደውን ወጣ ገባና ምቹ ያልሆነ መንገድ ማቀራረጥ ያልቻሉት እኒሁ ሴት ልጆች ናቸው።

በእፍረትና መሸማቀቅ አሊያም ሊደርስባቸው ከሚችል መደፈርና የኃይል ጥቃት ለመጠበቅ በሚል በቤተሰቦቻቸው ከቤት እንዳይወጡ በር የሚዘጋባቸው እኒሁ አካል ጉዳተኛ ሴት ልጆች ናቸው።

በአዳጊ አገሮች አካል ጉዳተኛ ልጆች የሚደርስባቸው መገለል ደረጃውና ዓይነቱ የከፋ ነው። ይኸው ማግለልም የመንግሥታቱ ድርጅት ዘላቂ የልማት ግቦችን የማሳካቱን ጥረት ጥያቄ ውስጥ የሚጥል ነው። ይህም ሁሉ ሆኖ ግን ጉዳዩ ሊሰጠው የሚገባውን ያህል ትኩረት እያገኘ አለመሆኑ ያሳስባል።

በዓለም ዙሪያ አካል ጉዳተኞች ከአንድ ቢሊዮን በላይ ብንሆንም ከፖለቲካው፣ ከመገናኛ ብዙኃኑ ከንግድ ተቋማትና ከሥራዎች እንድንገለል መሆኑ እንደሌለን ያክል እንድንቆጠር አድርጎናል። ለዚህም ነው በፈረንጆቹ አቆጣጠር ዲሴምበር 3 ቀን ማለትም ጎዳር 24 ቀን በየዓመቱ የሚከበረው የዓለም አቀፍ አካል ጉዳተኞች ቀን ድምፃችንን ለማሰማት እጅግ ጠቃሚ ቀን የሚሆነው።

በአካል ጉዳተኛ ልጆች ላይ የሚደርሰው መገለል ሊቆም ይገባል። ሁሉም ሕፃናት እኩል የትምህርት ዕድል ሊያገኙ ይገባል። ምቹ ሁኔታ ከተፈጠረላቸው አካል ጉዳተኞችም ድንቅ ሥራ ሠርተው ማሳየት ይችላሉ እያልን ድምፃችንን ከፍ አድርገን ልንናገር ይገባል።

አንድ ነገር ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ልሞክር። ምንም እንኳ እኔ ባልፍበትም በተለይ አካል ጉዳተኞች ለብቻቸው ለማስተማር የሚቋቋሙ ትምህርት ቤቶች ለችግሩ መፍትሔ እንዳልሆኑና ያንንም እንደ መፍትሔ እያቀረብኩ እንዳልሆነ ይሰመርልኝ። እነዚህ ‹‹ልዩ›› ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተደራሽ አይደሉም። ከገንዘብም አንፃር አዋጭነታቸው እጅግ ዝቅተኛ ነው። እንደ መንግሥታቱ ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) መረጃ እነዚህ ልዩ ትምህርት ቤቶች አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን አካተው ከሚያስተምሩ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ጋር ሲነፃፀሩ በአሥራ አምስት እጥፍ ውድ ናቸው።

የመጨረሻ ግባችን ከልዩ ትምህርት ቤቶች ይልቅ ሁሉም ልጆች፤ ወንዶችም ሴቶችም፣ አካል ጉዳተኞች ሆኑም አልሆኑ በአንድ ክፍል ውስጥ እኩል የሚማሩበት የአካቶ ትምህርት ሥርዓትን መፍጠር ሊሆን ይገባል። አካታች የትምህርት ሥርዓት የአካል ጉዳተኞች መገለል እንዲያበቃ ለማድረግና ከትምህርት ቤት ውጭ ያሉ ሕፃናትን ቁጥር በእጅጉ ለመቀነስ የሚያስችለን ሁነኛ መንገድ ነው።

ሆኖም በቅርብ ይፋ የሆነው ‹‹ኮስቲንግ ኢኪውቲ›› የተሰኘ ጥናት የሚያሳየው ለአካቶ ትምህርት ማስፈፀሚያ ከመንግሥታት፣ ከለጋሽ ድርጅቶች፣ እንደ አውሮፓ ኅብረትና ‹‹ግሎባል ፓርተነርሺፕ ፎር ኢጁኬሽን›› ያሉ የረዥም ጊዜ የአካቶ ትምህርት ደጋፊዎችም ቼምር የሚመድቡት ገንዘብ እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነ ነው።

እነዚህ የለውጡ አቀጣጣይ መሆን የሚገባቸው ተቋማትና አካላት የበጀት አመዳደባቸውንና ቅድሚያ ስለሚሰጡት ጉዳይ በድጋሚ ማሰብ የሚገባቸው ይመስለኛል። በአዳጊ አገሮች የሚገኙ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ወጣት አካል ጉዳተኞች ለመማርና ተቀጥረው ለመሥራት ፈቃደኞች ቢሆኑም ይህን ማድረግ በሚጠይቀው ውድ ዋጋ ምክንያት ፈቃዳቸው ሊሳካ አልቻለም።



ነገር ግን እንደባንግላዴሽ፣ ካምቦዲያ፣ ህንድ፣ ኔፓልና ፊሊፒንስ ያሉ አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው በአካል ጉዳተኞች ትምህርትና ሥልጠና ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት አዋጭነት ጉዳት ለሌለባቸው ተማሪዎች ከሚፈሰው ሙሳለ ንዋይ አዋጪነቱ ከሁለት እስከ ሦስት እጥፍ ይበልጣል።

ስለሆነም ዋነኛ ለጋሽ ተቋማት ከትምህርት ጋር ለተያያዙ ፕሮግራሞች ለሚሰጡት በጀት አካታችነትን እንደ ቅድመ ሁኔታ ቢወስዱ ከፍተኛ ለውጥ ይመጣል ብዬ አስባለሁ። ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች መንግሥታት ለትምህርት የሚይዙትን በጀት ለመጨመር ቢስማሙና ትምህርት ቤቶቻቸው ሁሉ አካታችና ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ አካል ጉዳተኛ ልጆች ከትምህርት ክፍሎች እንዲገቡ ምቹ ሁኔታ ቢፈጥሩ ትልቅ እመርታ ልናይ እንችላለን።

አካል ጉደተኛ ልጆች እኩል የሆነ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ብናደርግ ምን ያህል አቅም እንደምንፈጥር አስቡት እስቲ? እኔ ትምህርት ቤት መሄዴን እንደ ዕድለኝነት እቀጥረዋለሁ። ቀጣይ ትውልድ የሆኑት አካል ጉዳተኛ ልጃገረዶችና ሴቶች ግን ከዚህ በተለየ መልኩ ትምህርትን ለጥቂቶች ብቻ እንደሚሰጥ ልዩ ዕድል ሳይሆን እንደ መሠረታዊ መብታቸው የሚቆሙለት እንዲሆን እመኛለሁ።"

እሷ የውስጧን መንገድ በመምረጥ በርካቶች በእሷና ከእርሷ በተሻለ መንገድ እንዲወጡ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንቅስቃሴ በማድረግ ለብዙሃኑ በር ከፍታለች። ይህን ትጋቷን እና ብርታትዋን የተመለከቱ ታላላቅ ዕውቅናዎችን ሰጥተዋታል።

ከእነዚህም መካከል የመጀመሪያውን አለም አቀፍ ሽልማት በ2003 እ.አ.አ አሚኒቴር የሚባል በሴቶች ጤና ላይ የሚሰራ ተቋም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪ በነበረችበት ወቅት በስነ ተዋልዶ እና የኤች አይቪን እንቅስቃሴ አስመልክቶ በግቢው ውስጥ ባስመዘገበችው ትልቅ ሥራ በአለም አቀፍ ደረጃ (አሚኒቴር አዋርድ) ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ሽልማት አግኝታለች። ከዚያም በክረምት ወቅት በአክሽን ኤይድ በሰብአዊ መብት አንቅስቃሴ ውስጥ በብዙ መልኩ ባደረገችው አስተዋጽኦ፤ በፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስ እንቅስቃሴ በአዲስ አበባ በቀድሞ አጠራር ሀብኮ በሚባል ድርጅት ሽልማት ተበርክቶላታል። በመቀጠል እ.አ.አ በ2011 በአለም አቀፍ ደረጃ (TIAW) ቲአው ተጽእኖ መፍጠር የቻሉ 100 ሴቶች ተብለው ከተሸለሙት ውስጥ አንዷ ነች፤ እንዲሁም በ2015/16 እ.አ.አ ደቡብ አፍሪካ በሚገኘው ሲኢኦ ኮሚዩኒኬሽን በአፍሪካ በበጎ አድራጎት ዘርፍ ‹‹ተጽእኖ ፈጣሪ ሴት›› በሚል ፤ በ2017 እ.አ.አ የራይት ላይቭሊሁድ ሽልማት ሎሪየት እና በ2018 እ.አ.አ ስፕሪት ኦፍ ሄለን ኬሌር ሽልማትን ስትቀበል ሌሎችንም የተለያዩ ሽልማቶችን እና ዕውቅናዎችን በዓለም አቀፍ ደረጃ እና ከአገር ውስጥ በ2009 ዓ.ም በዊንድስ ኮሙዩኒኬሽን ‹‹ የኢትዮጵያ ሴት ልጃገረዶች መልካም አርአያ›› ሽልማት ተሰጥቷታል፤ ከነዚህ ሽልማቶች በተጨማሪ ታሪኳ አስተማሪ ነው ተብሎ ተምሳሌት የሚል መጽሀፍ ላይ ‹‹የኢትዮጵያ 100 ስኬታማ ሴቶች›› ላይ ሰፍሯል፤ እንዲሁም ህንደኬ ፅኑ የኢትዮጵያ ሴቶች የሚል መፅሀፍ ላይ ከታተሙ ‹‹10 ስኬታማ ሴቶች›› ውስጥ ገብታለች።

እሷ የትነበርሽ ንጉሴ የኢትዮጵያዊያን ሴቶች ልክ ማሳያ ሆና በሁሉም ሰፍራ ትነሳለች። ወጣቶችን በማነቃቃት የመልካም ስብዕና ግንባታ ትምህርቶችን በማስተማር የለውጥ ተምሳሌት ሆናለች። ከእነዚህ አገልግሎቶቿ በተጨማሪ አሁን ላይ በብሔራዊ ዕርቀ ሰላም ኮምሽን ለአገራዊ ሰላም እና አንድነት በመስራት ላይ ትገኛለች።

በልጅነቷ የዓይንዋን ብርሃን ብታጣም ውስጣዊ ብርሃንዋን በማውጣት ለብዙዎች ብርሃን ሁናለች። ሕይወት የትጋትና የልፋት ውጤት መሆንዋን ፤ ፍላጎት እስካለን ድረስ ጠንክረን በመስራት ያሰብነውን ሁሉ ልናሳካው የምንችል መሆኑን አረጋግጣልናለች። ሴትነትን ከፍ አድርጋ ደምቃበታለች። ስለ-ሷ አርአያነቷን እንዲህ አቀረበች።

